## የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያን
## <u>እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ</u>

የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

መመሪያው ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያን (እንደገና) ለማሻሻል የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ማሻሻያ

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. የመመሪያው አንቀጽ 6(5) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 6(5) ተተክቷል።

"6(5) በአዋጁ አንቀጽ 35 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በዓለም ዐቀፍ ግልፅ ጨረታ የሚፈፀመውን ግዥ ጨምሮ የግዥው የገንዘብ መጠን በዚህ ንዑስ አንቀጸ ከተገለፀው እና ከዚያ በላይ የሆነን ግዥ የጨረታ ማስታወቂያው በጋዜጣ በወጣበት ተመሳሳይ ጊዜ በኤጀንሲው የመረጃ መረብ (ድረ ገፅ) ላይ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ) | ለግንባታ ሥራ | ከብር | 20,000,000 | በላይ |
| ለ) | ለዕቃ | ከብር | 6,000,000 | በላይ |
| ሐ) | ለምክር አገልግሎት | ከብር | 4,000,000 | በላይ |
| መ) | ለሌሎች አገልግሎቶች | ከብር | 2,000,000 | በላይ" |

2. ከመመሪያው አንቀጽ 16.8.6 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 16.8.7 ተጨምሯል።

"16.8.7 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 16.8 እንደተጠበቀ ሆኖ በግንባታ ሥራ ግዥ ዘርፍ የሚጠየቀው የሥራ ልምድና የብቃት መስፈርት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ "6" ከተመለከቱት መስፈርቶች ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል።"





አብዱልአዚዝ መሐመድ
ሚኒስትር

የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር *

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ) | ለግንባታ ሥራ | ከብር | 150,000,000 በላይ |
| ለ) | ለዕቃ | ከብር | 50,000,000 በላይ |
| ሐ) | ለምክር አገልግሎት | ከብር | 7,500,000 በላይ |
| መ) | ለሌሎች አገልግሎቶች | ከብር | 21,000,000 በላይ” |

5. የመመሪያው አንቀጽ 21.1 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 21.1 ተተክቷል፡፡

“21.1 የመንግሥት መ/ቤት የምክር አገልግሎት ግዥን የመወዳደሪያ ሀሳብ በመጠየቅ መፈፀም ያለበት እና የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ከብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺ.ህ ብር) በላይ ሲሆን፣ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 መሠረት ግዥውን የፍላጐት መጠየቂያ ጥሪ በማካሄድ መፈፀም አለበት፡፡”

6. የመመሪያው አንቀጽ 22(1) መንደርደሪያ ተሠርዞ በሚከተለው ተተክቷል፡፡

“22.1 የመንግሥት መ/ቤት የምክር አገልግሎት ግዥው ግምታዊ ዋጋ ከብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺ.ህ ብር) የሚበልጥ በሚሆንበት ጊዜ፣ በምክር አገልግሎቱ አቅርቦት ለመሠማራት ፍላጐት ያላቸውን ዕጩ ተወዳዳሪዎች በመጋበዝ ጥሪ ማድረግ ይኖርበታል፡፡”

7. የመመሪያው አንቀጽ 23.3 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 23.3 ተተክቷል፡፡

“23.3 ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 23.2 የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በአዋጁ አንቀጽ 49.2 መሠረት በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ መጠቀም የሚቻለው የሚገዛው የግንባታ ዘርፍ ሥራ፣ ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት ወይም አገልግሎት ጠቅላላ ዋጋ ከሚከተለው የማይበልጥ ሲሆን፣ ብቻ ነው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ) | ለግንባታ ሥራ | ብር | 6,000,000 |
| ለ) | ለዕቃ | ብር | 1,500,000 |
| ሐ) | ለምክር አገልግሎት | ብር | 900,000 |
| መ) | ለሌሎች አገልግሎቶች | ብር | 1,200,000 |

ሠ) የግንባታ ዕቃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚሆንበት የግንባታ ሥራ ውል ለግንባታ ዕቃዎች ግዥ ተግባራዊ የሚሆነው ለግንባታ ሥራ ግዥ የተፈቀደው የገንዘብ ጣሪያ ይሆናል፡፡”

አብዱልአዚዝ መሐመድ
ሚኒስትር

የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

8. የመመሪያው አንቀጽ 24.2 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 24.2 ተተክቷል፡፡

"24.2 ከሚከተለው የገንዘብ መጠን የማይበልጥ እና በዋጋ በማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የሚፈፀም ግዥን ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚወክለው ሰው እንዲፀድቅ በማድረግ ግዥ መፈፀም ይቻላል፡፡

ሀ) ለግንባታ ሥራ እስከ ብር 500,000
ለ) ለዕቃ እስከ ብር 200,000
ሐ) ለምክር አገልግሎት እስከ ብር 120,000
መ) ለሌሎች አገልግሎቶች እስከ ብር 150,000

ሠ) የግንባታ ዕቃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚሆንበት ጊዜ ለግንባታ ዕቃዎች ግዥ ተግባራዊ የሚሆነው ለግንባታ ሥራ ግዥ የተፈቀደው የገንዘብ መጠን ይሆናል፡፡"

9. የመመሪያው አንቀጽ 25(7) (ሀ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 25(7) (ሀ) ተተክቷል፡፡

"25(7)(ሀ) የመንግሥት መ/ቤት በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር) ያልበለጠ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከመፍታት ጋር የተያያዙ የቀጥታ ግዥዎችን ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት መፈፀም ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈፀሙ ጥቃቅን ግዥዎች ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺህ ብር) መብለጥ አይኖርበትም፡፡"

## 3. <u>ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በግንባታ ሥፍራ ላይ ለሚገኙ የግንባታ ዕቃዎች ስለሚከፈለው ክፍያ የሚደነግገው አንቀጽ 16.26.10 ተፈፃሚ የሚሆነው ይህ መመሪያ ተፈፃሚ ከሚሆንበት ቀን ጀምሮ ተገዝተው ወደግንባታ ሥፍራ ለሚገቡ ዕቃዎች ብቻ ነው፡፡

*አዲስ አበባ ታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም.*

*አብዱልአዚዝ መሐመድ*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር*

የጤ/ግ.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር ሕ/ክ/2/59
Ref. No.
ቀን 14/04/2008
Date

**ዝርዝራቸው ከዚህ ጋር አባሪ ለሆኑ የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች**
**በያሉበት**

የፌዴራል መንግሥት ግዢ ስለሚፈፀምበት አኳኋን በገንዘብ መጠን ተወስነው የተቀመጡት ገደቦች ከወቅቱ የገንዘብ የመግዛት አቅም ጋር እንዲጣጣሙ፣ በግዢ አፈፃፀም አድልዎ እንዲኖር በር የሚከፍቱ አንቀፆች እንዲስተካከሉ፣ እንዲሁም ለፕሮጀክቶች በወቅቱ መጠናቀቅ አጋዥ የሚሆኑ አሠራሮች ሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ በፌዴራል መንግሥት የግዢ አፈፃፀም መመሪያ ላይ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡

ስለዚህ የመመሪያውን ማሻሻያ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ ከታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አብዱልአዚዝ መሐመድ
ሚኒስትር

ግልባጭ
ለመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ
አዲስ አበባ

Lettt.W/GT

ስልክ
TEL 251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83,86,89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
ፋክስ
Fax.251-11-155 13 55,55 14 96
251-11-155 38 44
አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia